መስከረም 2004 ዓ.ም

# ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ ሲዳሰስ

ክፍል ሶስት፣

# የኢሮብ ህዝብ መሰረቱ ከየት ነው?

ከበየነ ገብራይ

በዚህ በክፍል ሶስት በዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ የተተረከው ዶኩመንታሪ ፊልም ውስጥ የኢሮብ ህዝብ መሰረት ወይም ታሪካዊ አመጣጥ ከትግራዊያን ነው የሚለው ትረካ ትክክል አለመሆኑን ለማሳየት እሞክራለሁ።

በዶኩመንታሪ ፍልሙ በዛሬው መጣጥፌ የምተችበት ዓረፍተነገር ተራኪው አቶ ጸጋው ታደሰ እንዲህ በማለት በትግርኛ ያስቀምጡት ላይ ይሆናል። እጠቅሳለሁ፣ ***"ህዝቢ ኢሮብ ታሪካዊ ፍሰቱ ብዘይምቁራጽ ዝፈልጥ፣ ቅድሚ አሽሓት ዓመታት ዝነበረ፣ ብዘይ ሓላፍ ዘላፍ ሓረግ ትውልዱን ታሪካዊ አመጻጽኣኡን ዘለፍፍ ዘርኢ ተጋሩ ካብዝኾኑ ህዘቢ ኢዩ"።*** ይላሉ።

***"የኢሮብ ህዝብ ታሪካዊ አመጣጡን ያለማቋረጥ የሚያውቅ፣ ከብዙ ሺ ዓመታት በፊት የነበረ፣ ያለምንም ማዛባት የትውልድ ሀረጉንና ታሪካዊ አመጣጡን የሚዘረዝር ከትግራዊያን ዘር የሆነ ህዝብ ነው።"***(ትርጉም የኔ)

በዶኩመንታሪ ፍልሙ ***"ህዝቢ ኢሮብ ታሪካዊ ፍሰቱ ብዘይምቁራጽ ዝፈልጥ፣ ቅድሚ አሽሓት ዓመታት ዝነበረ፣ ብዘይ ሓላፍ ዘላፍ ሓረግ ትውልዱን ታሪካዊ አመጻጽኣኡን ዘለፍፍ ዘርኢ ተጋሩ ካብዝኾኑ ህዘቢ ኢዩ"።*** የሚለው ታሪክ በጥናት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በአፈ-ታሪክ ደረጃ ባንዳንድ አባቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲነገር የመጣ ብቻ እንደሆነ የያንዳንዱ የዛሬ የኢሮብ ብሄረሰብ አባላት የሆን ሰዎች የትውልድ ሀረጋችንን ወደ ኋላ የተወሰኑ ትውልዶችን በመቁጠር በምናገኛቸው ስሞች፣ በህልና አኗኗር የብሔረ-ሰቡ አመጣ ከየት እንደሆነ ጠቃሚ ምልክቶችን በቀላሉ ለማግኘት ይቻላል ባይ ነኝ። እንዴት የሚለውን እኔ በዛሬው መጣጥፌ በዝርዝር የምሄድበት ሲሆን በቅድሚያ ግን ለያንዳንዳችሁ የኢሮብ ብሄረሰብ አባላትም የሚከተለውን ጥያቄ ራሳችሁን በመጠየቅ ራሳችሁ መልስ እንድትሰጡበት እጠይቃለሁ።

***ያንተ/ቺ የዘር ሀረግ ወደ ኋላ ስትቆጥር/ሪ ምን ያህል %ቱ ከትግራዊያን፣ ከሓዶ፣ ከዳብሪመላ፣ ከጋዓሶ.....ወዘተ. ይዛመዳል/ይመሳሰላል ?***

የሩቅ የኢሮብ ህዝብ መሰረት/ታሪካዊ አመጣጥን በተመለከተ በአፈ-ታሪክ ደረጃ የተለያዩ አፈ-ታሪኮች ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉልን እንደመጡ ሁላችን የሚናውቀው ሃቅ ነው። ስለነዚህ አፈ-ታሪኮች ምንነትና በተለያዩ አበው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ

የመጡትን አፈታሪኮች ምን እንደሚመስሉ አቶ ኃይለስላሴ ዮሃንስ **ስለ ኢሮብ ህዝብ ታሪክ ያልተመለሱ ጥያቄዎች** በሚል ርእስ፣ እንዲሁም አቶ ግርማይ ተስፋገርጊስ **የኢሮብ ታሪክ ጥያቄዎችና አባባሎች** በሚል ርእስ በሶስት ክፍሎች በመክፈል የጻፉዋቸውን መጣጥፎች ትክክለኛ የኢሮብ ህዝብ መሰረት ከየት እንደሆነ በጥናት ላይ ተመስርቶ ታሪኩን ለመጻፍ ለሚፈልግ ሰው ጥሩ መነሻ ሊሆኑ የምችሉና ሌሎችም ሊቀጥሉበት የሚገባ ጅማሮ ናቸው።

በዶኩመንታሪ ፍልሙ የኢሮብ ህዝብ መሰረት ከትግራዊያን ነው የሚለው በጥናት ላይ ያልተመሠረተ ትረካ ሆን ተብሎ ታሪክን ለማዛባት፣ መጻኢው ትወልድ ስለ መሰረቱ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዳይዝ ለማድረግ ሆን ተብሎ በህወሓት አመራር የተቀነባበረ መሆኑ ሲታወቅ፤ እኔን ዛሬ ግራ እያጋባኝ ያለው፣ አንዳንድ የኢሮብ ብሄረሰብ አባላትም ይህን የዶኩመንታሪ ፍልም ትረካን የሚደግፉ መጻህፍት በመጻፍ ላይ መገኘታቸው ነው።ስለሆነ እውነተኛ የኢሮብ ህዝብ ታሪክ ሳይዛባ እንዲጻፍ የሚፈልጉ ወገኖች ከምጊዜም በላይ ነቅተው ሁኔታውን እንዲከታተሉና መውሰድ የሚገባቸው የማስተካከያ እርምጃ ጊዜ ሳይወስዱ እንዲወስዱ የሚገባበት ወቅት ላይ መገኘታችን ለሁሉም ግልጽ መሆን አለበት። ይህ የኢሮብ ህዝብ ታሪክን ከፖሊቲካና ከሃይማኖት እምነት ጋር በመያያዝ መጻፍ፣ በፊልም ደረጃ መቀረጽ አብዛኛው የኢትዮጵያ ታሪክ ከገጂዎቹ መሳፍንቶች ፍላጎትና እምነት ጋር በማያያዝ ከተጻፈው ጋር የሚመሳሰል አደገኛ ታሪካችንን የማዛበት ጉዞ እንዳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል። ስለሆነም ታሪካችን እንደ ታሪክ ሳይዛባ እንዲጻፍ የምንፈልግ ወገኖች ታሪክ ለፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ፕሮፓጋንዳ መሳሪያነት ሲውል ይህ ትክክል አይደለም ማለት መቻል ይኖርብናል።

ወደ ተነሳሁበት ርእሰ ጉዳዬ ልመለስና **እውነት የኢሮብ ህዝብ መሰረቱ/ታሪካዊ አመጣጡ በዶኩመንታሪ ፍልም አቶ ጸጋው እንደሚተርኩልን ከትግራዊያን ነው?** በሚለው ጥያቄ በመጠየቅ ልጀምር፣

ይህን ጥያቄ ከላይ ባስቀመጥኩት መሰረት እያንዳንዳችሁ ራሳችሁን በመጠየቅ ልትመልሱት የሚገባ መሰረታዊ ጥያቄ መሆኑን በድጋሚ ላስምርበት እወዳለሁ። ለውይይቱ መነሻ እንዲሆነን ግን እኔ ጥያቄውን ከራሴ የትውልድ ሀረግ በመነሳት ለማሳየት ልሞክር።

እኔ ከየተኛው ብሄረሰብ ነህ ከተባልኩ መልሴ ከኢሮብ ብሄረሰብ ነኝ የሚል ይሆናል። የዘር ሃረግህስ ከየት ነው ከተባለ ደግሞ ባባቴ ወገን ሳሆ ተናጋሪ ከሆኑ ከጋዓሶና ከዳብሪመላ ነኝ። በናቴ ወገን ደግሞ የናቴ አባት ትግርኛ ተናጋሪ ከሆኑ ከሱሩኩሶ ሲሆኑ፣ የናቴ እናት ደግሞ ከያቦ ኩማኒት ዲክ /ኢሮብ እና ከሓዶ/ዓሳዓሊላ ነው፣ ነው መልሱ። እኔ ዛሬ ራሴን በኢሮብ ብሄረሰብ አባልነት ሳስቀመጥና በኢሮብነቴ ስኮራ ከጋዓሶ፣ ዳብሪመላና ሓዶ ያለኝ የዘር ሀረጌን ረስቼ ወይም እንዳለ ፍቄ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም/አይገባም። እንደኔ የዘር ሀረግ ያላቸው በርካታ የዛሬ ኢሮቦችም ልክ እንደኔ እንደሚያስቡ ፈጽሞ ጥርጣሬ ውስጥ መገባት የለበትም። ሌላም ዛሬ እኔና መሰሎቼ የካቶሊክ/ክርስትና እመነት ተከታይ ነን። የጥንቱን ትተን ከቅርብ አያቶቻችን አብዛኛዎቹ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ እንደነበሩም በግልጽ መታወቅና መቀመጥ አለበት። ስለዚህ ዶኩመንታሪ ፍልም እኔንና መሰሎቼን፣ እጠቅሳለሁ፣ ***"ህዝቢ ኢሮብ ታሪካዊ ፍሰቱ ብዘይምቁራጽ ዝፈልጥ፣ ቅድሚ አሽሓት***

***ዓመታት ዝነበረ፣ ብዘይ ሓላፍ ዘላፍ ሓረግ ትውልዱን ታሪካዊ አመጻጽኣኡን ዘለፍፍ ዘርኢ ተጋሩ ካብዝኾኑ ህዘቢ ኢዩ"።*** ምንም ጥናት ሳያካሂድና የተነሳበትና የደረሰበት የጥናት መላምትም ሆነ የጥናቱ መነሻና መድረሻ ሳይገልጽ እንዲሁ በደፈና ሊለን ፈጽሞ አይችልም/አይገባምም እላለሁ።

የኢሮብ ህዝብ መሰረቱ/ታሪካዊ አመጣጡ ከትግራዊያን ብቻ አይደለም የምለው እኔ ብቻ አይደለሁም። አቶ ግርማይ ተስፋገርጊስም <u>የኢሮብ ታሪክ ጥያቄዎችና አባባሎች</u> በሚል ርእስ በተከታታይ በኢሮብ ማብሎ ባወጡዋቸው መጣጥፎቻቸው በክፍል ሶስት በገጽ 4 የዛሬ የኢሮብ ህዝብ በተለይ ከሓዶ ጋር ሰፊ የዘር ሀረግ ግኑኝነት እንዳለው እንደሚከተው በግልጽ አስቀምጧል።
እጠቅሳለሁ፣ "በኢሮብ ውስጥ ከሓዶ የማይወለድ ያለ አይመስለኝም። ይህም ሓዶና ኢሮብ ከጥንት ጀምረው ተመላልሰው ስለተጋቡ ነው። በኢሮብና ሓዶ መካከል የተፈጸፀሙ ጋብቻዎችና ግኑኝነቶችን ሁለ እዙህ መጥቀስ ባይቻልም የተወሰኑት የጥንቶቹን ልጥቀስ፦
1) ሓሳባላ መጀመርያ ዋራ የምትባል የሓዶ ተወላጅን በኋላ ደግሞ ዒሳ የምትባል የዋራ ወንድም ልጅን አግብቶ መላው ሓሳባላን ወልዷል። ስለዚህ በዚህ መልክ ሓሳባላ በሙለ የሓዶ ተወሊጆች ናቸው ማለት ነው።
2) የቡክናይታ አራተኛ ልጅ የሆነው ኣፍራሃ-በዐራ ማሊካ የምትባል የሓዶ ተወላጅን አግብቶ ከአስሚዒ-ፊረ በስተቀር ሞላው ቡክናይቲ-ዓረን አፈራ፤ አስሚዒ-ፊረም በኋላ ከሓዶ ጋር ተጋብተዋል። ስለዚህ በቡክናይቲ-ዓረም ከሓዶ የማይወለድ የለም ማለት ነው።
3) አድጋዲ-ዓረ ውስጥም የሓዶ የዘር ሓረግ የሌለው ያለ አይመሰለኝም። ለምሳሌ የብዘዎቹ የአድጋዲ-ዓረ ህዝብ ቅድመ-አያት የሆነው ኣውዓላ የሓዶ ተወላጅ የሆነችው ሥልጣናን አግብቶ ወልደገረጊስ፣ ዓንደገርጊስ፣ ሓያሎም፣ ዳቱ፣ አፍራሓና ማናን… ወልዷል። ሌሎች የአድጋዲ-ዓረ ነገዶችም እኔ ባላውወቅም እንደሌሎች የኢሮብ ነገዶች ከሓዶ ጋር ደጋግመው ተጋብተው ለሆኑ ይችላሉ።
ይህን የኢሮብና የሓዶ መዋለድን በሚመለከት አቶ ሚኪኤል ገብራይ የተባሉ የኢሮብ ተወላጅ በሳሆ ቋንቋ በገጠሙት አጭር ግጥም እዘጋዋለሁ።

**ዮኮሊክ ቃይሲ ያም ሒነ**
**ዮኮሊክ ሰክቲ ያም ሒነ**
**ሓዲ አቡሳ ኪክ ኒነ**
**ሓዲ ኒ አቡሳ ኪክ ዪነ**
**አማይ ማሕለ መዐም ኒነ"።** ይላሉ።

እኔም እያንዳንዱ ዛሬ ራሱን የኢሮብ ብሄረሰብ አባል ነኝ ብሎ/ላ የሚያስቀምጥ/የምታስቀመጥ የዘር ሀረጉ/ጓ ትንሽ ወደኋላ በመሄድ ቢመረመር ከትግራዊያን ይልቅ ከሓዶና ሌሎች ሳሆ ተናጋሪ ከሆኑ አጎራባች ጎሳዎች ይበልጥ መሰረት እንዳለው/ላት ምንም ጥርጥር የለኝም። ልክ የተከበሩ አቶ ሚካኤል ገብራይ እንዳሉትም፣

ዮኮሊ ቃይሲ ያም ሒነ

ዮኮሊ ሰክቲ ያም ሒነ

ሓዶ፣ ጋዓሶከ ዳብሪመላህ …ወዘተ. አቡሳ ኪክ ኒነ

ኣማይማሕለ መዐም ኒነ። እላለሁ።

**መደምደሚያ**፣ ይህ ያልተዳሰሰ የኢሮብ ህዝብ ታሪክ በሚል የተሰራው ዶኩመንታሪ ፊልም ሆነ የኢሮብ ህዝብ መሰረቱ ከትግራዊያን ነው የሚለው በአንዳንድ የብሄረሰቡ አባላትም እየተደገፈ ያለው አባባልና አጻጻፍ በዚች ባሁኗ ወቅት መውጣት ሆን ተብሎ የኢሮብ ህዝብ ታሪክ ከፖሊቲካና ከሃይማኖት ጋር በማያያዝ የብሄረ-ሰቡ ትክክለኛ ታሪካዊ አመጣጥ ከፖሊቲካና ከሃይማኖት ጋር በማያያዝ ለፖልቲካዊና ሃይማኖታዊ ፕሮፖጋንዳቸው መሳሪያነት ለመጠቀም ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ሴራ ነው እላለሁ። ከዚህ በተጨማሪም ዶኩመንታሪ ፍልሙ ሆነ ስለ ኢሮብ ህዝብ መሰረቱ ከትግራዊያን ነው በማለት አሁን እየተጻፉ ያሉት መጻህፍት በዚች ባሁኗ ወቅት መውጣት ዝም ብሎ በድንገት የተገጣጠሙ ናቸው ብዬ እኔ አላምንም። እንደ እኔ እምነት ብሄረሰቡን ለመከፋፈልና ብሎም ለማዳከም በህወሓት መሪዎችና ደጋፊዎቻቸው የተቀነባበረ ሴራ ነው እላለሁ።

ለዚህ በማስረጃነት ሊጠቀሱ ከምችሉት በዚህ ባሳለፍነው 20 ዓመታት በኢሮብ ወረዳ ከተፈጸሙት የተለያዩ ተግባሮች፣

1. የኢሮብ ወረዳ ዋና ከተማን ከዓሊተና ወደ ዳውሃን መቀየር
2. በሻዕቢያ ወረራ ጊዜ በሻዕቢያ ተጠልፈው የተወሰዱና እስከዛሬ ድረስ አድራሻቸው የማይታወቁ ከ100 በላይ የሆኑ ንጹሃን የኢሮብ አርሶ አደሮች በተመለከተ እስከዛሬ ድረስ እንደ መንግስት አንድም ነገር ትንፍሽ አለማለት
3. የኢሮብ ህዝብ ለዘመናት ሲኖርበት የነበረውና አንድም ቀን የኤሪትራ አካል ሆኖ የማያውቅ የኢትዮጵያ መሬት አሳልፎ ለሻዕያ መስጠት በዋናነት ሊጠቀሱ የምችሉ ናቸው።

በመጨረሻም፣

1. ታሪክን በተመለከተ፣ ታሪካችን ሳይዛባ እንዲጻፍ ችሎታው ያለችሁ ወገኖች ከምንጊዜም በላይ ታሪካችንን ለመጻፍ መስራት በሚገባችሁ ወቀት ላይ መሆናችን መረዳት አለባችሁ እላለሁ።
2. የኢሮብ ብሄረሰብ መሰረቱ ከየትም ይሆን ከየት ዛሬ ምንም እንኳን የተዳከመ ቢሆንም አሁን እንደ አንድ የራሱ ቋንቋ፣ ባህልና የተወሰነ የኢሮብ ህዝብ መኖሪያ ተብሎ የሚታወቅ ጂዮግራፊያዊ አከባቢ ይዞ የሚኖር አንድ ራሱን የቻለ ብሄረሰብ እንዳለ የሚቀበል/ምትቀበል፣ ይህ ብሄረሰብ ህልውናው እንዲቀጥል የሚፈልግ/የምትፈልግ ቅን አመለካከት ያለው/ላት ፖለቲካዊ ሆነ ሃይማኖታዊ እምነትን ወደ ጎን በመተው፣ ከጥላቻ በመራቅ፣ ከግል ፍላጎትና ጥቅም ይበልጥ የብሄረሰቡን ፍላጎት በማስቀደም ማንኛውም የዚህ ብሄሰብ ህልውና መቀጠል የሚጎዱትን ተግባሮች ከየት ይምጡ ከየት በጋራ ልንታገለው በሚገባን አሳሳቢ ወቅት ላይ መሆናችንን ላሳስብ እወዳለሁ።

ከኔ ጋር ለሚደረገው ግኑኝነት የሚከተለውን አድራሻ መጠቀም ይቻላል፣

beyene54@yahoo.com